ገቢዎች ሚኒስቴር

# መመሪያ ቁጥር 189/2017

# የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ

የካቲት 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# መመሪያ ቁጥር 189/2017

# የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ

የታክስ ባለሥልጣኑ የቅጣት ይነሳልኝ ማመልከቻ ሲቀርብለት ወይም በራሱ ተነሳሽነት በታክስ ከፋይ ላይ የተጣለን አስተዳደራዊ ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ሊያነሳ እንደሚችል በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ፤

ቀድሞ ሥራ ላይ በነበረ የቅጣት አነሳስ መመሪያ ያልተሸፈኑ አስተዳደራዊ ቅጣቶች እንዲካተቱ ማድረግ፣ የቅጣት አነሳስ ሁኔታው ፍትሃዊ እንዲሆን ማድረግ እና ቅጣቱን ስለሚያነሳ የሥራ ክፍል በይበልጥ ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 115(4) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር 189/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

ለዚህ መመሪያ አፈጻፀም የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

1/ "የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል" ማለት በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 55(1) በአዋጁ መሰረት በባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተቋቋመ፣ በአስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ ላይ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ በማጣራት ለቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ የዉሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የስራ ክፍል ነው።

2/ "ጨረታ" ማለት የታክስ ዕዳን ባለመክፈል በታክስ ባለስልጣኑ የተያዘን ንብረት በግልጽ ጨረታ ሥነ-ሥርዓት የመሸጥ ሂደት ነዉ።

3/ "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት ታክስ ከፋዩ በራሱ ሊያስወግደዉ የማይችል የተፈጥሮ ወይም ሰዉ ሰራሽ አደጋ ወይም ጽኑ ህመም ወይም ታክስ የመክፈልና ሌሎች ግዴታዎችን እንዳይወጣ የሚያደርግ ግልጽ ምክንያት ነው።

4/ "ጽኑ ህመም" ማለት ታክስ ከፋይ ወይም የታክስ እንደራሴው የዉሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰዉ ወይም አስታውቆ መክፈል ባለበት ጊዜ ዉስጥ ተንቀሳቅሶ መስራት የማያስችል ህመም ላይ ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል እውቅና ያገኘ የህክምና ተቋም በህክምና ማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ በጊዜው የንግድ ስራ እንቅስቃሴዉን የሚመራለት የታክስ እንደራሴ ወይም ወኪል የሌለው ሲሆን ነው።

5/ "የቅጣት ደረጃ ምደባ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የሚነሳ አስተዳደራዊ ቅጣትን ለመወሰን ሲባል በታክስ ህጎች የተዘረዘሩትን አስተዳደራዊ ቅጣቶች ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ደረጃ በማለት የተደለደለበት የቅጣት ምደባ ደረጃ ነው።

6/ "የታክስ ባለስልጣን" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ሲሆን፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮዎችን ይጨምራል።

7/ "አዋጅ" ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው።

8/ በታክስ አስተዳደር አዋጅ እና በታክስ ህጎች ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች እንደአግባብነታቸው በዚህ መመሪያ ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በታክስ ህግ መሠረት በተጣለ የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## አስተዳደራዊ ቅጣት የሚነሳበት ሁኔታ እና መጣኔ

4. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት የሚነሳበት እና የማይነሳበት ሁኔታ</u>

1/ በዚህ መመሪያ የአንቀጽ 12 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በታክስ ህግ የተጣለ አስተዳደራዊ ቅጣት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6፣ 7 እና 10 መሰረት በከፊል ወይም በሙሉ ሊነሳ ይችላል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በአዋጁ አንቀጽ 108፣ 113 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 አንቀጽ 66(1)(ሰ) የታክስ ደረሰኝ

ካለመስጠት ጋር በተያያዘ የተጣለ ቅጣት እና በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 10(3) መሠረት የተጣለ ቅጣት የሚነሳ አይሆንም።

5. <u>የአስተዳደራዊ ቅጣቶች ደረጃ ምደባ</u>

በአዋጁ መሰረት የተጣለ አስተዳደራዊ ቅጣት የድርጊቱ መፈፀምና አለመፈፀም በታክስ አስተዳደር ስርዓቱ ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ እና የታክስ ዕዳው የተከፈለበትን ጊዜ መሰረት በማድረግ አስተዳደራዊ ቅጣቶች በከፊል የሚነሱበት ቀጥሎ በተዘረዘረው መሰረት ቅጣቶችን በዝቅተኛ ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ደረጃ በመመደብና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 በተደረነገገው መስፈርትና መጣኔ ስንጠረዥ መሰረት ቅጣቱ የሚነሳ ሆኖ፡-

1/ የአዋጁ አንቀጽ 101 ፣ 103 ፣ 109 እና 112 በዝቅተኛ የቅጣት ደረጃ ፤

2/ የአዋጁ አንቀጽ ፣ 105 ፣ 106 እና 114 (ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 6) ፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 አንቀጽ 38(1) እስከ (3) የተጣለ ቅጣት በመካከለኛ የቅጣት ደረጃ ፤

3/ የአዋጁ አንቀጽ 102፣ 104፣ ፣ 107፣ 110፣ 111 እና 114(7) ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 አንቀጽ 66 ቅጣት በከፍተኛ የቅጣት ደረጃ ተመድበዋል።

4/ በዚህ መመሪያ የቅጣት ደረጃ ምደባ ያልተሰጠው ማንኛውም የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት በተደነገገበት የታክስ ህግ ላይ የማይነሳ መሆኑ ተገልጾ እስካልተገደበ ድረስ በመካከለኛ የቅጣት ደረጃ ተመድቦ የሚስተናገድ ይሆናል።

6. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል የሚነሳበት መስፈርትና መጣኔ</u>

ከላይ በአንቀጽ 5 በተደነገጉት የቅጣት ደረጃዎችና የታክስ ዕዳው የተከፈለበትን ጊዜ እና ሁኔታ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ በተገለፀው መሰፈርትና መጣኔ መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣቶች በከፊል ሊነሱ ይችላሉ፤

| ተ.ቁ | ፍሬ ታክስ፣ ወለድ እና የማይነሳውን ቅጣት የተከፈለበት ጊዜ | የሚነሳው ቅጣት ምጣኔ በቅጣት ደረጃ ምደባ መስረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ቅጣት | በመካከለኛ ደረጃ የሚመደብ ቅጣት | በከፍተኛ ደረጃ የሚመደብ ቅጣት |

Ethiopian ... Records & Doc... No 1

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ታክስ ከፋዩ የታክስ ዉሳኔ ማስታወቂያ ወይም በቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት የተሰጠ የታክስ ማስታወቂያ በደረሰዉ በ30 ቀን ውስጥ ቀርቦ፡- | | | |
| 1.1 | ሙሉ በሙሉ ከከፈለ | 90 | 80 | 70 |
| 1.2 | ከባለስልጣኑ ጋር በሚያደርገው እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ውስጥ ከከፈለ | 80 | 70 | 60 |
| 1.3 | ከባለስልጣኑ ጋር ባደረገው ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ውስጥ ታክሱን ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| 2 | ታክስ ከፋዩ የታክስ ዉሳኔ ማስታወቂያ ወይም በቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት የተሰጠ የታክስ ማስታወቂያ በደረሰዉ ከ31 እስከ 60 ቀን ባለው ጊዜ ታክሱ ከተከፈለ፡- | | | |
| 2.1 | ሙሉ በሙሉ ከከፈለ | 80 | 70 | 60 |
| 2.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| 2.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ፣ | 60 | 50 | 40 |
| 3 | ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ወይም በቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት የተሰጠ የታክስ ማስታወቂያ ደርሶት የሚፈለግበትን ታክስ ሳይከፍል 60 ቀን ካለፈው በኋላ ቀርቦ፡- | | | |
| 3.1 | ሙሉ በሙሉ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| 3.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ውስጥ ታክስ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| 3.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 50 | 40 | 30 |
| 4 | ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ባለመክፈሉ ሀብቱ ከተያዘ በኋላ ነገር ግን የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ ቀርቦ፡- | | | |

Records & Docu

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4.1 | ሙሉ በሙሉ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| 4.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 50 | 40 | 30 |
| 4.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 40 | 30 | 20 |
| 5 | ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ባለመክፈሉ በሀብቱ ላይ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣ በኋላ ቀርቦ ታክሱን ከከፈለ ፦ | | | |
| 5.1 | ሙሉ በሙሉ ከከፈለ | 50 | 40 | 30 |
| 5.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 40 | 30 | 20 |
| 5.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠዉ ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ስምምነት ጊዜ ከከፈለ | 30 | 20 | 10 |

7. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ የሚነሳበት ሁኔታ፤</u>

1/ ከዚህ ቀጥሎ በተገለጹ ምክንያቶች በታክስ ከፋዩ ላይ የተጣለ አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ ሊነሳ ይችላል፦

ሀ) ታክስ ከፋዩ የታክስ ግዴታውን በመክፈያ ጊዜው እንዳይከፍል የሚያደርግ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ያጋጠመው ከሆነ፤

ለ) የድርጅቱ የንግድ ሥራ ሊቀጥል የማይችል እና የከሠረ (bankrupt) መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፤

ሐ) ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋዩን ሒሳብ ከመመርመሩ በፊት ታክስ ከፋዩ ስህተቱን በራሱ ተነሳሽነት ያረመ እንደሆነና በተሻሻለው የታክስ ስሌት መሠረት ፍሬ ታክስና ወለድ ከከፈለ፤

መ) ከንብረቱ 20 በመቶ እና ከዚያ በላይ በተፈጥሮ ወይም በሰው አደጋ ሰራሽ ምክንያት የወደመበት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም ያቀረበ ከሆነ፤

ሠ) ከራሱ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የሚያስቀር ተቀጣሪ በሥራ ላይ እያለም ሆነ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ፤

ረ) ለቅጣቱ ምክንያት የሆነው የታክስ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በፈጠረው የአሰራር ስህተት መሆኑ ከተረጋገጠ።

ሰ) ከወርሃዊ ማሳወቂያ ጋር በተያያዘ በመክፈያ ጊዜው ግብር ከፋዩ ባንክ ገቢ በሚያደርግበት ጊዜ በወቅቱ ቀርቦ ደረሰኝ ባለማስቆረጥ ምክንያት በሲስተም የሚሰላው ቅጣት፤

2/ ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ወይም የግብር ይግባኝ ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ በደረሰው 30 ቀናት ውስጥ ታክሱን ወለድ እንዲሁም በመካከለኛ ወይም በከፍተኛ ደረጃ የማይነሳውን ቅጣት ሙሉ በሙሉ ከከፈለ በታክስ ውሳኔ ውስጥ የሚገኝና በዝቅተኛ ደረጃ የተመደበ አስተዳደራዊ ቅጣት ካለ ሙሉ በሙሉ ይነሳል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው ቢኖርም ፍሬ ታክስና ወለድ ሳይኖር የተወሰነው ውሳኔ መቀጫ ብቻ ከሆነ ታክስ ከፋዩ የሚስተናገደው በመመሪያው አንቀጽ 6(1) (1.1) መሠረት ነው።

4/ በከፍተኛ እና በመካከለኛ ደረጃ የተመደበ መቀጫ ባይኖርም ከታክስና ወለድ ጋር በዝቅተኛ ደረጃ የተመደበ መቀጫ የተወሰነ ከሆነ ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ወይም የግብር ይግባኝ ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ግብሩንና ወለዱን ሙሉ በሙሉ ከከፈለ በዝቅተኛ ደረጃ የተመደበው መቀጫ ሙሉ በሙሉ ይነሳል።

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ቢኖርም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ነው።

8. <u>የቅጣት ይነሳልኝ ጥያቄ አቀራረብ</u>

1/ አስተዳደራዊ ቅጣት የተወሰነበት ሰው ቅጣቱ እንዲነሳለት ምክንያቱን በመግለጽ ለባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ለታክስ ዕዳ አስተዳደር የሥራ ሂደት መሪ ወይም ለታክስ ኦፕሬሽን የሥራ ሂደት መሪ ወይም ለታክስ ማዕከል አስተባባሪ በጽሑፍ ማመልከት አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የገቡ ፍሬ ታክሱን፣ ወለዱንና የማይነሳውን ቅጣት ከፍለው ከጨረሱ ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልግ ቅጣቱ የሚነሳ ይሆናል።

9. <u>ቅጣትን የማንሳት ሥልጣን</u>

1/ የታክስ ዕዳ አስተዳደር የሥራ ሂደት አስተባባሪ፣ የታክስ ኦፕሬሽን የሥራ ሂደት መሪ ወይም የታክስ ማዕከል አስተባባሪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 እና 7 መሠረት ቅጣት ሊያነሱ ይችላሉ።

2/ አስተዳደራዊ ቅጣቱ ስለመነሳቱ ለዚህ አላማ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶ በሥራ ሂደቱ ከተረጋገጠና ከጸደቀ በኋላ የሚከፈለው ታክስ፣ ወለድና የማይነሳው የቅጣት መጠን ተከፍሎ

Ethiopian ... Records & Do... ...tion No 1

ቀሪው ቅጣት ዕዳውን በሚከታተለው የዕዳ ክትትልና አሰባሰብ ባለሙያ በሥራ ላይ ባለው ሲስተም መሰረት ተገቢው መግለጫ ሰፍሮ እንዲሰረዝ ይደረጋል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በሚነሳው ቅጣት ላይ በታክስ ከፋዩ የሚቀርብ ቅሬታ በቅ/ጽ/ቤቱ የተቋቋመው የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ሥራ ክፍል ቅሬታውን በመቀበልና በመመርመር ለቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የውሳኔ ሃሳብ አቅርቦ ይወሰናል።

10. <u>አስተዳደራዊ ቅጣትን በልዩ ሁኔታ ስለማንሳት</u>

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4(2)፣ 6 እና 7 ላይ የተመለከተው ቢኖርም በኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊ ወይም ማህበራዊ ምክንያቶች የታክስ ባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ወይም የሚወክለው ኃላፊ በታክስ ከፋዩ ጥያቄ መሠረት ወይም በታክስ ባለሥልጣኑ የራስ ተነሳሽነት መሠረት የተጣለን አስተዳደራዊ ቅጣት በልዩ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊያነሳ ይችላል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ ሁኔታ የሚታይ የቅጣት ይነሳልኝ ጥያቄ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት መቅረብ ያለበት ሲሆን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ጥያቄውን ከታክስ ከፋዩ የሚፈለግ ጠቅላላ የታክስ ዕዳ መጠን፣ የታክስ አይነት፣ የታክስ ዕዳው ያለበት ሁኔታ፣ የታክስ ከፋዩ የታክስ አከፋፈል ታሪክ፣ በልዩ ሁኔታ ቅጣት እንዲነሳ የተጠየቀበትን ተጨባጭ ምክንያትና ማስረጃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው ምክንያት ስለመሆኑ ተረጋግጦ ዝርዝር የውሳኔ ሃሳብ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጁ ተፈርሞ ለታክስ ባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ወይም የበላይ ኃላፊው ለሚወክለው ሰው መላክ አለበት።

3/ የታክስ ባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ወይም የበላይ ኃላፊው የሚወክለው ሰው በልዩ ሁኔታ የአስተዳደራዊ ቅጣት ይነሳልኝ ጥያቄ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተቀብሎ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ እንዲሁም የግብር ከፋዩን ጥያቄ እና ስለጉዳዩ የቀረበውን ማስረጃ መርምሮ አስተዳደራዊ ቅጣቱ በልዩ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ወይም ቅጣቱ እንዳይነሳ የውሳኔ ሀሳብ እንዲቀርብ ለታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ይልካል።

4/ ለታክስ ባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ወይም ለሚወክለው ሰው ቀርቦ በሚወሰነው ውሳኔ መሠረት እንዲፈጸም በታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በኩል ለቅ/ጽ/ቤቱ የሚላክ ሆኖ የሚነሳው አስተዳደራዊ ቅጣት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9(2) መሠረት ተፈጻሚ የሚደረግ ይሆናል።

5/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ውሳኔ ሲሰጥ ቅጣቱን በልዩ ሁኔታ ለማንሳት ጥቅም ላይ የዋለው ማስረጃ በአግባቡ ያልታየ ከሆነ የታክስ ባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በድጋሚ ሊያየው ይችላል።

Ethiopian ... Records ...

11. <u>ለቅጣት አነሳስ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ስለሚፈጸምበት ሥርዓት</u>

1/ የታክስ ዕዳውን በተራዘመ ጊዜ ለማስከፈል ከግብር ከፋዩ ጋር በሚደረግ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ውስጥ ከፍሬ ታክስና ወለድ በተጨማሪ በዚህ መመሪያ መሠረት የማይነሳው ቅጣት ብቻ ተጨምሮ ሊነሳ የሚችለው ቅጣት እንዳይካተት ሊደረግ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው አግባብ ግብር ከፋዩ በስምምነቱ መሠረት ፍሬ ታክሱንና ወለዱን ከፍሎ ማጠናቀቁ ሲረጋገጥ ቅጣቱ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

3/ በስምምነቱ መሠረት ግዴታውን ካልተወጣ ቅጣቱ በቀጣይ ባልተከፈለ የታክስ ዕዳ መጠን መሠረት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌ</u>

12. <u>ወለድ የማይነሳ ስለመሆኑ</u>

1/ በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ እና በሌሎች የታክስ አዋጆች መሰረት በዘገየ የታክስ እና የግብር ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ በዚህ መመሪያ መሠረት ሊነሳ አይችልም፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በህግ ወለድ መሰላት በሌለበት ሁኔታ በታክስ ጉዳይ ላይ በታክስ መረጃ ሥርዓቱ ወይም ሲስተም ባህሪ የተነሳ ተሰልቶ የሚገኝ ወለድ ጉዳዩ በሚመለከተው ባለሙያ መግለጫ እንዲቀርብ ተደርጎ ከሲስተም ላይ እንዲሰረዝ በቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጁ ሲወሰን ተገቢው መግለጫ ሰፍሮ ከሲስተም ላይ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

13. <u>ሪፖርት ስለማቅረብ</u>

1/ ቅ/ጽ/ቤቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ፣ 7 ፣ እና 10 ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሱ ውሳኔ የተሰጣቸው አስተዳደራዊ ቅጣቶች መጠን በየወሩ ተጠናቅሮና በግልጽ ተለይቶ ከወርሃዊ ሪፖርት ጋር ለታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት መቅረብ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶች ሪፖርታቸውን እንዲልኩ የታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ክትትል ያደርጋል እንደአስፈላጊነቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው ዘርፍ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

3/ የታክስ ባለስልጣኑ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲነሳ ውሳኔ የሰጠበትን የእያንዳንዱን መዝገብ መረጃ በማጠናከር በየሩብ አመቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No 1

14. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>

በሥራ ላይ የነበረው የታክስ አስተዳራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር 137/2010 እና ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሰርኩላርና ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል።

15. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በመመሪያ ቁጥር 137/2010 መሠረት ተቀባይነት አግኝቶ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ውስጥ ገብቶ የታክስ ዕዳውን በመክፈል ላይ የሚገኝ ግብር ከፋይ የአስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ ጉዳይ በነባሩ መመሪያ መሠረት ፍጻሜ ያገኛል።

16. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በገቢዎች ሚኒስቴር ድህረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ፤ የካቲት 2017 ዓ.ም

አይናለም ንጉሴ አሊ

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር

# Directive no 189/2025

## A directive on waiving of tax Administrative penalty

WHEREAS, as it is stipulated in the tax administration proclamation that the tax authority may waive all or part of the administrative penalty imposed on taxpayer as per this directive when an application for the waiving of penalty is submitted by the tax payer or by the initiative of the tax authority;

WHEREAS, it is necessary to incorporate additional provisions to address omitted administrative penalties, ensure fairness in the application of penalty waivers, and clarify the roles and responsibilities of the departments involved in the waiver process;

NOW, THEREFORE, the ministry of revenues has issued this directive under the authority given by the Federal Tax Administration proclamation No. 983/ 2016 Articles 115(4)

## Part 1

## General Provisions

1. **Short Title**

   This directive may be cited as "Tax Administrative Penalty waiving directive no. 189/2025"

2. **Definition**

   In this directive, unless the context otherwise requires:

   1/ "Tax decision objection reviews department" means the office established within the tax authority's branch office in accordance with the federal Tax Administration Proclamation no.983/2016, Article 55(1), which reviews and submits a recommendation to the branch manager when an objection filled against a decision on the waiving of the administrative penalty.

   2/ " Auction" means the process of selling property seized by the tax authority for non-payment of tax liability in accordance with the tax law through an open tender procedure.

   3/ "Force majeure" means a natural or man-made disaster or severe illness that the tax payer cannot avoid, or a real and proven reason that impedes from paying taxes and other obligations.

Records & Docu... ation No 1

4/ "Severe illness" means a tax payers or tax representative or an agent who received a notice of decision could not move or work at the time of declaration or payment due to severe illness that has to be certified by medical institution which is recognized by relevant body.

5/ "Penalty level classification" means the level of penalty classification in which the administrative penalties listed in the tax laws are classified as low, medium and high level in order to determine the administrative penalty that will be waived as per this directive.

6/ "Tax authority" mean the ministry of revenues and include the revenue offices of Addis Ababa and Dire dawa city Administration.

7/ "Proclamation" means the Federal tax administration Proclamation No. 983/2016

8/ Words and phrases defined in the federal administration Proclamation and tax laws shall apply, mutatis mutandis, to this directive.

### 3. Scope of Application

This directive shall apply to tax administrative penalties imposed under the tax laws.

## Part Two

## Rates and conditions to waive administrative penalty

### 4. Waivable and non-Waivable administrative penalties

1/ Subject to the provisions of Article 12 of this directive, administrative penalties imposed by the tax law may be waived in whole or in part in accordance with article 6, 7 and 10 of this directive.

2/ Notwithstanding the provisions of sub- article 1 of this article, the administrative penalty imposed in connection with failure to issue a tax receipt in accordance with Article 108,113 and value added tax proclamation number 1341/2024 Article 66(1)(g) and Article 10(3) of the stamp duty proclamation number 110/1990 shall not be waived.

### 5. Classification of the level of Administration penalties

The penalty imposed as per the tax law may be waived partially depending on its impact on the tax administration system and the time that the tax debt has been paid. Hence, to waive the penalty in line with article 6 of this directive each penalty shall initially be leveled as low, medium and high as follows:

1/ penalties as per Article 101,103,109 and 112 of the proclamation are classified as lower level of penalty.

2/ Penalties imposed as per Article, 105,106 and 114 (from sub article 1 to 6) of the proclamation, Article 38(from sub article 1 to 3) of excise tax proclamation number 1186 is classification as medium level of penalties.

3/ Penalties imposed as per Article 102,104፣107, 110,111ለ and 114(7) of the proclamation; Article 66 of the value added proclamation number 1341/2016 are classified as high level of penalties.

4/ any tax administrative penalty that its level of classification is not assigned in this directive shall be classified as a medium level penalty unless it is specified as non waivable penalty under the tax law.

**5. Criteria and rate of partial waiving of administrative penalty.**

Depending on the classification of the level of penalty stated under Article 5, administrative penalty may be partially waived based on the time and Status of the tax debt being paid as per the criteria and rate described below;

| N.O | Time of payment of tax, interest and non- waivable penalty | The waivable penalty depending on the classification of penalty level in percent is | | |
|---|---|---|---|---|
| | | Low level of penalty | Medium level of penalty | High level of penalty |
| 1. | If the tax payer pays the tax as follow within 30 days of receiving a tax assessment notice or a decision made by tax review department or tax appeal commission or the court; | | | |
| 1.1 | fully paid | 90 | 80 | 70 |
| 1.2 | within the payment agreement period of up to 6 months with the tax authority | 80 | 70 | 60 |
| 1.3 | within payment agreement period of more than 6 months with authority | 70 | 60 | 50 |



Ethiopian Minis... Records & Docu... No 1

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2. | If the tax payer pays the tax as follow with 31 to 60 days of receiving the tax assessment notice or based on the decision by review department or the tax appeal commission or the court decision: | | | |
| 2.1 | fully paid | 80 | 70 | 60 |
| 2.2 | within the payment agreement period of up to 6 months with the authority | 70 | 60 | 50 |
| 2.3 | Within the payment agreement period of more than 6 months with tax authority. | 60 | 50 | 40 |
| 3. | If the tax payer pays the tax as follow after 60 days of receiving the tax assessment notice or based on the decision by review department or the tax appeal commission or the court decision; | | | |
| 3.1 | fully paid | 70 | 60 | 50 |
| 3.2 | within the payment agreement period of up to 6 months with tax authority | 60 | 50 | 40 |
| 3.3 | within the payment agreement period of more than 6 months with the tax authority | 50 | 40 | 30 |
| 4 | If the tax payer pays the tax as follow after property has been seized for not paying the required tax, but the payment is held before the render notice is has been issued; | | | |
| 4.1 | fully paid | 60 | 50 | 40 |
| 4.2 | within the payment agreement period of up 6 months with tax authority | 50 | 40 | 30 |
| 4.3 | within the payment agreement period of more than 6 months with the tax authority | 40 | 30 | 20 |
| 5 | If the tax payer pays the required tax as follow after the tender notice has been issued on the property seized due to failure of paying tax; | | | |



በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር የሰነዶችና ማስረጃዎች
Ethiopian Ministry of Revenues Records Documentation No 1

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 5.1 | fully paid | 50 | 40 | 30 |
| 5.2 | within the payment agreement period of up to 6 months with tax authority | 40 | 30 | 20 |
| 5.3 | within the payment agreement period of more than 6 months with the tax authority | 30 | 20 | 10 |

**6. The situation in which the administrative penalty will fully waived**

1/ Administrative penalties imposed on the tax payer may be fully waived for the following reasons:

a) At the time that the tax payer is unable to pay the tax on time due to force majeure.

b) When the tax payer's business cannot continue and it is confirmed by the court that the business is bankrupt.

c) The tax error is corrected by taxpayer's own initiative before the tax authority examines the accounts of the taxpayer and if the taxpayer paid the tax and interest in accordance with the assessment.

d) When the taxpayer submits evidences from the relevant government institute stating that 20 percent or more of the property has been destroyed due to natural or man-made dangers.

e) An employee who withholds tax from his own income, whether he is working or when his employment contract is terminated

f) When it is confirmed that the administrative penalty is the tax authority's operational error.

g) The penalty calculated by the system due to tax payer's failure to file a receipt on time after the tax payment is remitted the tax to the bank during the payment period in relation to the monthly declaration.

2/ when the tax payer pays the tax and interest as well as the non-waivable penalty in the medium and high level of penalty within 30 days of receiving the notice of the tax assessment or the decision of review department or the court decision; the penalty assigned at low level shall be fully waived

...opian Ministry of Revenues
Records & Documentation No 1

3/ Notwithstanding the provisions of sub- article 2 of this article, the tax decision is only a penalty without main tax and interest, the tax payer shall be treated as per article 6(1)(1.1) of this directive

4/ The decision without high or medium level penalty but with low level penalty accompanied by tax as well as interest and this tax and interest is fully paid within 30 days of receiving the assessment notice of the tax or the tax appeal or the court decision, the low level penalty shall be fully waived

5/ notwithstanding the provisions of sub-article 3 of this article, the applicability of the provisions of sub-article 1 of this article shall prevail.

**7. Procedure for penalty waving Application**

1/ The taxpayer that has been given an administrative penalty must apply in writing to the tax authority or tax debt management department or the tax center coordinator stating the reason for the waiving of the penalty,

2/ Notwithstanding the provision of sub-Article 1 of this article, the taxpayer that entered in to agreement to extend the payment period have already paid the tax, interest and non-waivable penalty, the penalty will be waived without the need to submit the application to the tax authority,

**8. The power to waive penalty**

1/ the tax authority or tax debt management department or the tax center coordinator may waive penalty as per article 6 and 7 of this directive,

2/ the waiving of administrative penalty shall be filled in a from prepared for this purpose and the process owner has been verified and approved that the tax, interest and non-waivable penalty amount have been paid and the remaining penalty shall be cancelled by tax debt collection and follow up officer by stating the relevant reason for cancellation.

3/ a complaint lodged by the taxpayers against the penalty waived in accordance with sub-article one of these articles shall be submitted to the tax review department that provides its recommendation to the manager of the branch.

**9. Waiving of the administrative penalty in special circumstances.**

1/ Notwithstanding the provisions of Article 4(2), 6 and 7 of this directive, for economic , administrative or social reasons, the head of the tax authority or his

representative may, at the taxpayer's request or by tax authority's initiative, fully or partially waive the administrative penalty in special circumstances.

2/ Subject to sub-article 1 of this article, a request for the waiving of penalty under special circumstances shall be submitted by the taxpayer to the branch office and the branch shall verify the total amount of tax debt required from the tax payer, the type of tax, the status of the tax payer, taxpayer's tax payment history, and the clear justification as well as evidence for requesting the waiving of penalty under special circumstances and the branch manager shall send the request to the head of the tax authority or the representative of the head with verification.

3/ the head of the tax authority or the representative of the head may send a request for the waiving of penalty under special circumstances which is verified as per sub-article 2 of this article to the directorate of the tax debt management for further verification and submission opinion on the request.

4/ the decision on waived penalty by head of tax authority or his representative shall be sent to the branch office through the directorate of tax debt management to be implemented as per Article 9(2) of this directive.

5/ the evidence used to decide on waiving of administrative penalty in special circumstance as per this article had not been verified properly, the head of the tax authority may see it again.

**10. The procedure for penalty waiving during installment payment agreement**

1/ In order to pay the tax debt in an extended period, in an installment payment period agreement with the taxpayer, in additional to tax and interest, only the penalty that is not waived according to this directive shall be added and the penalty that shall not be waived may not be included.

2/ Subject to sub-article 1 of this article after it is confirmed that the taxpayer has paid the tax, interest and non-waivable penalty in accordance with the agreement, the waivable penalty shall be waived.

3/ If the obligation is not fulfilled as per the agreement, the penalty shall be calculated based on the amount of unpaid tax debt.

## Part – Three

## Miscellaneous provisions

**12. Interest not subject to waivable**

1/ Pursuant to the federal income tax proclamation and other tax laws, interest assessed on deferred tax payments shall not be waived in accordance with this directive.

2/ Subject to sub-article 1 of this article, when interest is wrongly calculated due to the problem of Tax Administration System or SIGTAS, the case shall be submitted to the manager of the branch to be deleted from system based on the statement of the relevant expert, and the reason for deletion of the interest should be stated clearly.

**13 Reporting**

1/ The amount of the administrative penalties' that have been decided to be fully or partially waived according to Article 6,7 and 10 of this directive shall be summarized and clearly identified every month and submitted monthly to the directorate of tax debt management through the branch office.

2/ tax debt management directorate will monitor the branch offices to send their reports and this directorate may send the information that is given as per sub article 1 of this article to the relevant division of the tax authority for corrective action to be taken, as necessary.

3/ the tax authority shall submit quarterly reports to the ministry of finance by consolidating the waiving amount of administrative penalty.

**14 . Repealed laws**

The directive number 137/2010 on the waiving of the penalty, any circular and customary practices that are contrary to this directive are repealed.

**15. Transitional provision**

A taxpayer's issue which has been accepted, before this directive goes in to effect, according to directive no. 137/2010 and entered in to an agreement to extend the tax payment period and paying the tax debt, the case of waiving an administrative penalty shall be implemented as per the repealed directive.

**16. Effective date**

This Directive shall be effective from the date of its registration by the Ministry of Justice and its uploading on the website of the Ministry of Revenues.

**Addis Ababa; February 2025**

**Aynalem Nigusie Ali**

**Minister of the Revenues Ministry**